የግንቦት 7፤ የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ
Ginbot 7 Movement for Justice Freedom and Democracy
Tel +44 208 1335670 pr@ginbot7.org

ቀን ግንቦት 4 2001

ከግንቦት7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የተሰጠ መግለጫ

# የብአዴን አባላት ወያኔን በቃኝ የሚሉበት ሰአት አሁን ነው።

ወያኔ ሰሞኑን በሰራዊቱና በመንግስታዊ አስተዳደሩ ውስጥ ባሉ የብአዴን አባላት ላይ ዘርን መለያ ያደረገ መጠነ ሰፊ ጥቃት እያደረሰ ነው። ይህ ጥቃት የመጀመሪያው አይደለም። ያሁኑ ግን ከመቼውም የባሰ ነው። የባሰ የሚያደርገው እስካሁን ወያኔ ያሰራቸውና የሚያሳድዳቸው የብአዴን አባላት ቁጥራቸው ስለተበራከተ ብቻ አይደለም። ወያኔ በአስር ሽዎች የሚቆጠሩ የብአዴን አባላት፣ ‹‹ዘረኛነህና ዘራፊነትህ በቃን›› ብለው ቆርጠው ተነስተዋል በሚል ፍርሃት ከሰራዊቱና ከተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በማባረር የትም አውጥቶ ሊበትናቸውና ሊያጠፋቸዉ የተዘጋጀ መሆኑ ነው። ይህ ብቻ አይደለም። ብአዴን እወክለዋለሁ የሚለው የአማራ ክልል ህዝብም ‹‹እምቢ ለወያኔ ዘረኛነት›› ከሚሉ ልጆቹ ጋር በአንድነት ስለተፈረጀ፣ ለብአዴን አባላት የመጣው ጥቃት ለህዘቡ በቀጥታ የሚደርሰው እንደሚሆን የግንቦት 7 ንቅናቄ ጠንቅቆ ስለሚያውቀው ነው።

ዛሬ የብአዴን አባላት ተወልደው ካደጉበት ቀያቸው እንደ አውሬ እየታደኑ ነው። ቤተሰባቸውን ልጆቻቸውን ጧሪ ቀባሪ የሌላቸውን ወላጆቻቸውን እየተው እንደገና በረሃና ስደትን ቤታቸው እንዲያደርጉ ተገደዋል። በመለስ ዜናዊ አይን፣ ለእዚህ መከራ የተዳረጉት የብአዴን አባላት ወንጀል፣ ወያኔ ገና ስልጣን ላይ በወጣ ማግስት የወያኔን ዘረኛ አካሄድ በሚገባ መረዳታቸው ነው። መለስ ዜናዊና በብአዴን በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ በአሽከርና የሰገሰጋቸው የአመራር አባላት ዘረኛነትን በማራገብ ህዝብ እርስ በርሱ እንዲፋጠጥ በማድረግ፣ መለስ ዜናዊና ድርጅቱ ወያኔ የማእከላዊ መንግስት ስልጣንና የሃገሪቱን ሃብት በሙሉ በቁጥጥር ስር ለማዋል ያቀዱትን እኩይ እቅድ አስቀድመው በማየትና ተቃውሞዋቸውን ማሰማታቸው ነው። ብርጋዴር ጄነራል ተፈራ ማሞ የመጀመሪያው ተቃዋሚ ነበር። ዛሬ የሚታደኑት የብአዴን አባላት ይህ የጥቂት ዘረኞች እቅድ በስራ ላይ እየዋለ ስልጣን፣ ጉልበትና ሃብት ተጠቃሎ በወያኔ ዘረኞች እጅ ውስጥ ሲወድቅ እያዩ ዝምታን መምረጥ ያለፈለጉ ናቸው። እንደ ጥቂት የብአዴን መሪዎች ከወያኔ ለሚወረወር ፍርፋሪ ስብእናቸውን ያልሸጡ ናቸው። እንደ እነዚህ ጥቂት የብአዴን አመራር ምንደኞች ከወያኔ ለሚወረወር ፍርፋሪ ሲሉ፣ የአማራውን ክልል ህዝብ እግር ከወርች ጠፍንገዉ፣ ወያኔ በባርነት እንዲገዛዉ ለማድረግ መሳርያ አንሆንም በማለት፣ ለራሳቸውና ለወገናቸው ክብርና ነጻነት ሲሉ ስቃይን፣ መከራና ሞትን የመረጡ ናቸው።

የግንቦት 7 ንቅናቄ በወያኔ ዘረኛነት አፋኝነትና ዘራፊነት የተማረሩት ጥቂት የጦር መኮንኖችና የመንግስት ሰራተኞች እንዳልሆኑ ያውቃል፡፡ ከሁለት ሳምንት በፊት ወያኔ ‹‹መፈንቅለ መንግስት›› ያለው ቀጥሎም ‹‹ሽብርና የግድያ ሃሰብ›› እያለ ያሻውን ስም የሰጠው እሱ እንደሚመኘው ጥቂት ግለሰቦችን በማሰር ብን ብሎ የሚጠፋ እንዳልሆነ የግንቦት7 ንቅናቄ በሚገባ ያውቃል። የተጀመረው ትግል የወያኔን

ዘረኛነትና ዘራፊነት የሚቃወም በሽዎች የሚቆጠሩ የብአዴን አባላትና የአማራውን ክልል ወገናቸውን የሚያጠቃልል፣ እንዲሁም በተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ልብ ውስጥም የተጫረ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ለውጥ እንቅስቃሴ ነው።

የግንቦት 7 ንቅናቄ ለረጅም ግዜ በብአዴንና በሌችም በተለይ በኦህዴድ ውስጥ የወያኔን ዘረኛነት በመቃወም የተካሄዱትን ትግሎች፣ በእዚህም ትግል ውስጥ ግለሰቦችና ቡድኖች የከፈሉትን መስዋእትነት ያውቀዋል። በምርጫ 97 ‹‹ከዘረኛው ወያኔ የተሻለ አማራጭ ነው›› በማለት ለቅንጅት ድምጻቸውን በሰጡት የሰራዊቱ አባላት ላይ ወያኔ ያደረሰውን ግፍና በደል እናውቀዋለን። መለስ ዜናዊ ምርጫውን አጭበርብሮ በጉልበት በስልጣን ለመቀጠል ሲወስን የአንተ የግፍ መሳሪያ አንሆንም በማለታቸው ከስራቸው ተባረው ቤተሰቦቻቸው በረሃብ እንዲጠበሱ የተደረጉ የጦር መኮንኖችና የፖሊስ ሰራዊት አባላትና ባለሌላ ማእረጎች በሽዎች የሚቆጠሩ እንደሆኑ እናውቃለን። በእዚህ ድርጊታቸው እነዚህ የሰራዊቱና የፖሊስ አባላት ወገኖቻቸውን ያኮሩ ውድ ጀግኖቻችን ናቸው።

የተጀመረው ‹‹በቃኝ የወያኔ ዘረኛነት›› እንቅስቃሴ፣ ከብአዴንና ከአማራ ክልል አልፎ ሃገራዊ የሆነ ትርጉም አለው። አድሎንና ዘረፋን በማጥፋት፣ ለአድሎና ለዘረፋ እንዲያመች ሲባል ህዝብ በወያኔ የተገፈፈውን የነጻነትና የዴሞክራሲ መብቶች ማስከበሪያ መሳሪያ ነው። ዘረኛ አድሎንና ዘራፊነትን በመቃወም በሃገሪቱ ውስጥ በየአቅጣጫው የተለኮሰውን የአመጽ ትግል ማስቆሚያ፣ ዘለቄታነት ያለው ሃገራዊ ሰላምና መረጋጋት መፍጠሪያ ነው። አድሎና ዘረኛነት እያንገፈገፈው በመቶ ሽዎች የሚቆጠር ምሁር ሃገሩን እየጣለ፣ እውቀቱን ለፈረንጅ ለመሸጥ እንዳይሰደድ፣ በሃገሩ ተከብሮ የአስተማረውን ህዝብ እንዲያገለግል ማድረጊያው ብቸኛው መንገድ ነው። ህዝቦች እውነተኛ በሆነ መንገድ እራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር የሚችሉበትን፣ የአካባቢያቸውን ሃብት በዋንኛነት ለአካባቢያቸው ልማት ማዋል የሚችሉበትን፣ ዴሞክራሲዊ የሆነ የፖለቲካ ስልጣንና ፍትሀዊ የሆነ የሃብት ድልድል የሚያገኙበት ብቸኛ መንገድ ነው። በዘረኛነት ላይ የተመሰረተ አድሎ በሌለበት ሁኔታ አንዱ የእንጀራ ልጅ አንዱ እውነተኛ ልጅ ሆኖ የማይታይበት፣ አንዱ ህዝብ ወርቅ ሌላው ፋንድያ ተደርጎ የማይበላለጥበት ስርአት የሚወልድ ነው። የተጀመረው ንቅናቄ ዜጎች በእኩልነትና በመተሳሰብ ወያኔ አጥሮ ካስቀመጠላቸው የክልል እስር ቤት ውጭ ማየት የሚችሉበትን፣ በክልሎች ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ‹‹በማእከላዊ መንግስት ጉዳይም ያገባኛል›› በማለት አንድነታቸውን አጥብቀው ለጋራ ሃገራቸው ህልውና ደህንነትና ጥቅም በጋራ የሚቆሙበትን ሁኔታ የሚያጠናክር ነው።

ግንቦት ሰባት እንዲህ አይነቱ ከፍተኛ ሃገራዊና ወገናዊ እርባና ያለው ንቅናቄ ግቡን እንዲመታ የብአዴን አባላትና የአማራ ክልል ህዝብ ማድረግ የሚገባውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል ይላል። የተጀመረውን ንቅናቄ በሚገባ ተደራጅቶ በጥንቃቄ መመራት ይኖርበታል። ወያኔ ተራ በተራ ቆራጥ የብአዴንን አባላት እየለቀመ፣ የአማራው ክልል ህዝብ በወያኔ የተጫነበትን የባርነት ቀንበር ለመስበር የሚደፍሩ ጀግኖች እስከሚያጣ ድረስ ይህንን ህዝብ ሊያኮላሸው ያቀደውን እኩይ እቅድ ማክሸፍ ተገቢ ነው እንላለን። ከሁሉም በላይ ግን የብአዴን አባላትና የአማራው ክልል ህዝብ ማወቅ የሚገባቸው ያነሱት የነጻነት፣ የእኩልነትና የፍትሃዊነት አላማ ወያኔ ብብት ውስጥ ተቀምጠ የማይሳካ መሆኑን ነው። ተወደደም ተጠላም፣ ለመለስ አደግዳጊ የሆኑት የብአዴን አመራሮች ህሞቱ ኖራቸውም አልኖራቸውም፣ ከሁሉ አስቀድሞ የብአዴን አባላት መታገል ያለባቸው ወያኔ የዘረኛነቱና የዘራፊነቱ መሳሪያ በማድረግ አስካሁን ሲገለገልበት ከነበረው ኢህአዴግ ከሚባል፣ ወያኔ ጠፍጥፎ ከሰራው የውሸት ግንባር እራሳቸውን ማውጣት ይኖርባቸዋል።

ኢህአዴግ የተለያዩ ድርጅቶች ግንባር እስከሆነ ድረስ፣ የእነዚህ ግንባር አካል ነኝ የሚለው ወያኔ፣ የብአዴንን አባላትና ቤተሰቦቻቸውን፣ ከእዛም አልፎ የወያኔን ዘረኛነት የሚቃወመውን የአማራን ክልል ህዝብ የጥቃቱ አላማ አድርጎ እየተንቀሳቀሰ ብአዴን ከገዳዩ ብብት ውስጥ ተሸጉጦ የሚቀጥልበት ምክንያት ሊኖር አይገባውም። አበው ‹‹እዳሪ ላይ ቆሞ ገማኝ አይባልም›› ይላሉ። የጸረ ዘረኛነትና የጸረ-ዘራፊነት ትግል ከለየላቸው ዘረኞችና ዘራፊዎች ጉያ ውስጥ ተቀምጦ የሚደረግ አይደለም። ብአዴን እንደ አባል ድርጅት ራሱን ከኢህአዴግ የማውጣት መብት አለው። መብቱ የሚከለከልም ከሆነ ‹‹ራሴን አውጥቻለሁ›› የማለት ግዴታ አለበት።

የብአዴን አባላት የድርጅታቸው አስቸኳይ አጠቃላይ ስብሰባ እንዲጠራ በማድርግ ብአዴን ዘረኛ የሆነውን ወያኔ አክ ብሎ የተፋው መሆኑን ለመላ ሃገሪቱ ህዝብ ማሳየት አለበቸው። ወያኔ ከኪሱ አውጥቶ የማይከፍላቸው የመከላከያ ሰራዊቱ አባላትና የመንግስት ሰራተኞች፣ ወያኔ ከጎተራው ዝቆ የማይሰፍርለት የአማራ ክልል ህዝብ የወያኔን አጋርነት ለምን ይፈልጋል? እውነት እንነጋገር ከተባለ ማነው ማንን የሚፈልገው? ብአዴን ነው ወያኔን የሚፈልገው? ወይስ ሌሎቹ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች እነኦህዴድ ናቸው ወያኔን የሚፈልጉት? መለያየት ቢመጣ የሚጎዳው ማን ነው? ኢህአዴግን ሽፋን አድርጎ  የዘረፋና የዘረኛነት ፍላጎቱን የሚያራምደው፣ ከሚገባው በላይ የሃገሪቱን ስልጣንና ሃብት የተቆጣጠረው ወያኔ ነው ወይስ ብአዴን?  ይህ የሚያሳየው የወያኔ ዘረፋ ግፍና በደል መቀጠል የቻለው ብአዴን ኦህዴድና ሌሎችም ስለፈቀዱለት ስለሆነ የጸረ-ወያኔ ትግሉ አንዱ ገጽታ ራስን ከወያኔ ኢህአዴግ መለየት ብቻ ነው።

የአማራውን ህዝብ የጥቂት ዘረኞች ባርያ በማድረግ ለደረሰበት ውርደት፣ ስቃይና ዘረፋ ተጠያቂ እንሆናለን የሚሉ በሙስናና በንጹሃን ደም የተጨማለቁ ጥቂት የብአዴን አመራር አባላት ለወያኔ ጌቶቻቸው ባላቸው የቡችላ ታማኝነት ብአዴን ከኢህአዴግ እንዲወጣ አባላቱ የሚያቀርቡትን ጥያቄ የማይቀበሉ፣ ስብሰባ እንዲደረግ የማይፈቅዱ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይታወቃል። ስብሰባ ቢደረግም ይህንን ሃሳብ አምረው ሊቃወሙ ይችላሉ። ሰፊው የብአዴን አባል ይህንን የጥቂት የወያኔ አሽከሮች ሴራ በጣጥሶ ድርጅታዊ ነጻነቱን ማወጅ መቻል ይኖርበታል።

ይህ ነጻነት የታመቀውን የአካባቢውንና የአባላቱን ቀና ህልም፣ ብቃትና ችሎታ ፈንቅሎ እንዲወጣ በማድረግ በሃገራችን የዘረኛነትን ግብአተ መሬት የሚያፋጥን እንደሚሆን ግንቦት 7 ጥርጣሬ የለውም። ኦህዴድም ሆነ የደቡብ ህዝቦች ድርጅቶች በተመሳሳይ ሁኔታ ድርጅታዊ ነጻነታቸውን በማወጅ፣ በሃገሪቱ ውስጥና በየክልሉ የሚገኘውን ህዝብ የነጻነትና የመብት ጥማት ለማርካት ተመሳሳይ ርምጃ በመውሰድ ለትውልድ የሚተላፍ ታሪክ መስራት ይችላሉ የራሳቸውንም ህይወት ከወያኔ ባርነት የጸዳ፣ በሰብአዊ ክብርና ነጻነት የተሞላ ማድረግ ይችላሉ። ለእንዲህ አይነቱ ክቡር አላማ ከሚነሱት ጎን የግንቦት 7 ንቅናቄ ብቻ ሳይሆን የመላው ሃገሪቱ ህዝብና በወያኔ ዘረኛነት ወደ ሃገሩ እንዳይመለስና ሃገሩን ጥሎ እንዲሰድድ የተደረገው በሚሊዮኖች የሚቆጠረው በአለም ዙሪያ በስደት ተበትኖ የሚኖረው ህዝብ ድጋፍና ትብብር የማይለያቸው እንደሆነ ሊያውቁት ይገባል።

*ብአዴንና ሌሎችም ድርጅቶች ራሳቸውን ከዘረኛው ወያኔ/ኢህአዴግ በማግለል ‹‹በቃኝ ዘረኛነት! በቃኝ አድሎ ይበሉ!*

*ውድቀት አምባገነንትንና ዘራፊነትን በ80 ሚሊዮን ህዝብ ላይ ለጫኑት ጥቂት ጎጠኞች!*

*ድል ነጻነቴን ወይም ሞቴን ብለው ለተነሱና ለሚነሱ ጀግኖቻችን በሙሉ!*

የግንቦት 7፤ የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ
www.ginbot7.org